ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

የእኛ መዝገቦች እንደሚያሳዩት ልጅዎ **measles, mumps, and rubella (MMR፣ የኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ) ክትባታቸውን በወቅቱ አልወሰዱም።**

በፕሮግራማችን ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ **የኩፍኝ ወረርሽኝ** ከተከሰተ፣ የMMR ክትባታቸውን በወቅቱ ያልወሰደ ወይም የኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም (መከላከያ) ማረጋገጫ ማቅረብ የማይችል ማንኛውንም ሰው ለበሽታው ከተጋለጠበት የመጨረሻ ጊዜ ጀምሮ **እስከ 21 ቀናት ድረስ ቤት ውስጥ እንዲቆይ** የጤና ጥበቃ መምሪያ ሊያስገድድ ይችላል። ይህም የኩፍኝ በሽታ ስርጭትን ለማስቆም ይረዳል።

የMMR ክትባት ልጅዎን እና ሌሎችን ለመጠበቅ ከሁሉም የተሻለው መንገድ ነው። ልጅዎ በቅርብ ጊዜ ክትባቶችን ወስዶ ከሆነ፣ እባክዎን የተሻሻለ Certificate of Immunization Status (CIS፣ የክትባት ሁኔታ የምስክር ወረቀት) ቅጽ ያቅርቡ።

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ ነው እንዲሁም በፍጥነት ሊሰራጭ ይችላል። በተጨማሪም ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን የWashington State Department of Health (የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያን) ይጎብኙ፦ doh.wa.gov/measles።

ስለ ኩፍኝ በሽታ እና ስለ MMR ክትባት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከጤና እንክብካቤ ባለሙያዎ ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታዎታለን።

ከሰላምታ ጋር፣